የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)
Amara Survival For Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)

# “በጥቂቱ ያላመሠገነ በብዙው አያመሠግንም”

**5/8/19**

ሰሞኑን የዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን ማድረጉ አይዘነጋም:: በዚህ ስብሰባው ከድሮው እጅግ በተለየና ከኢሕአዴግ እህትና አጋር ድርጅቶች አመለካከት የተለየና ብአዴን/ኢዴፓ ከተመሠረተበት የሕወሓት ጉዳይ አስፈጻሚነት ዓላማ ተፃራሪ የሆነ አቋም ወስዶ ስብሰባውን ማጥናቀቁ በብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች ተገልጹዋል::

የክልሉ ምክር ቤት ይበል! በርታ! የሚያሰኘው የአቋም መግለጫ አብዛኛው የዐማራ ሕዝብ ላለፉት 28 ዓመታት “ሕገ-መንግሥቱ ዐማራን አይወክልም” “ሕገ-መንግሥቱ ፀረ ዐማራ እና የኢትዮጵያ አንድነት ነው!” በማለት ይቃወመው የነበረውን የሕዝብ ጥያቄ ተጋርቶ “ ሕገ-መንግሥቱ መሻሻል አለበት” በማለት የያዘው አቋም ነው::

ይህ አቋም “ለአንድ ክልል ብለን ሕገ-መንግሥት አንቀይርም” “በሕገ-መንግሥቱና በፌደራላዊ ሥርዓት አንደራደርም” የሚሉት ድምፆች በኢሕአዴግና በሕወሓት አመራሮች ጠንክሮ በሚነገርበት ሰዓት የዐማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ለእነዚህ ድምፆች ዋጋ ሳይሰጡ ለሕዝብ ድምፅ ጆሮ ሰጥተው የዐማራውና የኢትዮጵያ አንድነት ችግሮች ቁዋጠሮ የሆነው ሕገ-መንግሥት እንዲሻሻል ጥያቄ ማንሳቱና ለዚህም ዕውን መሆን ለመታገል መወሰናቸው ይበል!ግፉበት! በርቱ! የሚያሰኝ መልካም እርምጃ እንደሆነ የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ያምናል::

የዚህ እምነታችን መሠረቱም የክልሉን መንግሥት በበላይነት የሚመራው ብአዴን/አዴፓ በማን እንደተመሠረተ እነማን እንደመሩት ለምን ዓላማ ማስፈጸሚያነት እንደተደራጀ ስለምንገነዘብ ከዚያ ሁሉ ትብታብ ቁልፍልፍ የጥቅምና የሥልጣን ተጠቃሚነት ይልቅ ለሕዝብ ፍላጎትና ዓላማ መቆም በመምረጣቸው ነው:: እንኩዋን ለዘመናት ከተመሩበት የዓለም አመለካከትና አሠራራዊ ግንኙነቶች መውጣት ቀርቶ ከነበሩበት ቤት ወጥቶ ወደ አዲስ ቤት መግባት የቱን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን ስለምንረዳ ጭምር ነው::

ስለሆነም አዴፓ በያዘው አቋሙ እንዲገፋ ሌሎች አስፈላጊ ጥያቄዎችን አንስቶ ለዐማራው ኅልውና መጠበቅና ለኢትዮጵያ አንድነት መረጋገጥ በርትቶ እንዲሠራ ለእነዚህ ዓላማዎች እውን መሆን ዓላማ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ወገኖች በል! በርታ! ግፋ ! ሊሉት ይገባል እንላለን:: በትንሹ ያላመሰገነ በብዙ አያመሰግንምና ምስጋናችን ለዚህ አቋዋም ችረን ቀሪዎችን እንዲያስከትል አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳደር ለጉዞአችን ጠቃሚም ተገቢም ነው እንላለን::

**የዐማራው ኅልውና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!**